# ስለ “የሚኒሶታ አጠቃላይ ግምገማዎች (MCA)” መረጃ



## MCAs ምንድን ነው?

የሚኒሶታ አጠቃላይ ግምገማዎች (MCAs) በማንበብ፣ በሒሳብ እና በሳይንስ ላይ ያተኮረ በየአመቱ የሚሰጥ ግምገማ ነው። MCAs በሚኒሶታ አካዳሚክ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ ነው፣ ይህም በተወሰነ ክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች ምን ማወቅ እና ምን ማድረግ መቻል እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው።



## MCAsን የሚወስደው ማነው?

ሁሉም በሚኒሶታ የህዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች MCAsን ይወስዳሉ። የማንበብ እና የሒሳብ ፈተናዎች የሚሰጡት በክፍል 3 8 እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (የ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ MCAsን፣ የ 11ኛ ክፍል ተማሪዎች የሒሳብ MCAsን ይወስዳሉ) ውስጥ ነው። የሳይንስ MCAs የሚሰጠው በክፍል 5 እና 8 እና የህይወት ሳይንስ ወይም ባዮሎጂ ኮርሶችን በሚወስዱበት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክፍል ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ነው።



## ተማሪዎች MCAsን የሚወስዱት እንዴት ነው?

ተማሪዎች የማንበብ፣ የሒሳብ እና የሳይንስ MCAsን የሚወስዱት በመስመር ላይ (online) ነው። አንዳንድ ተማሪዎች በተናጠል ትምህርታዊ ዕቅዳቸው (Individualized Educational Plan (IEP)) ወይም በ 504 ዕቅዳቸው መሰረት ለወረቀት ፈተና ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።



## ተማሪዎች MCAsን የሚወስዱት ለምንድን ነው?

MCAs የወረዳዎች እና ትምህርት ቤቶች ካሪኩለም እና መመሪያ ከስቴት አካዳሚ መስፈርቶች ጋር ወጥ ስለመሆናቸው መረጃ ለመሰብሰብ ያገለግላል። ትምህርት ቤቶች የካሪኩለም ቁሳ ቁሶችን እና የተማሪ ድጋፍን ለማሻሻል መረጃውን ይጠቀማሉ። ትምህርት ሰጪዎች ተማሪዎች ጥሩ ያመጡበትን ቦታዎች የሚያስተምሩበትን መንገድ ለማጠናከር እነዚህን ቦታዎች ይፈልጋሉ። ትምህርት ሰጪዎች እንዲሁም መስፈርት ተኮር ካሪኩለም እና መመሪያን ማሻሻል የሚችሉባቸውን ቦታዎች ይፈልጋሉ።



የጨመረ የመረጃ ትክክለኛነት



በመረጃ የተደገፈ የወረዳ እና የትምህርት ቤት ውሳኔዎች

## በ MCAs ውስጥ መሳተፍ

የተማሪዎች በ MCAs ውስጥ መሳተፍ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም ትምህርት ቤትዎ እና ወረዳዎ ሁሉም ተማሪዎች የከፍተኛ ጥራት ትምህርት መዳረሻ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ካሪኩለማቸውን እና መመሪያቸውን የሚገመግሙበት እድል ይሰጣቸዋል። ብዙ ተማሪዎች በተሳተፉ ቁጥር ወረዳዎች እና ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ ገንዘብን እና ግብዓቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በመረጃ የተደገፈ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ መረጃው ይበልጥ ትክክለኛ ይሆናል።

ተጨማሪ መረጃ MDE ድር ጣቢያ ላይ ይገኛል

(ከ Students and Families > Programs and Initiatives > Statewide Testing ስር)።